**ዘመንና ቀመር**
አዲስ የምንለው ቀኑ፤ ወሩ፤ ዓመቱ
በጊዜ አቆጣጠር ቀመረ ስሌቱ
ቀድመን ኖረነዋል ነገን በትናንቱ።

ረዥሙ ጉዞ
መራራው ትግላችን፤ አንዱን አምባገነን
ቀይሮ በሌላ
ዓርባ ዓመት በሙሉ ህይዎት እየበላ
ዘመን ሲያስቆጥረን ድል እየሰነቀ
ይመጣል ያልነው ቀን ሄዶ ሄዶ አለቀ።

**መብትና ንግግር**
የንግግር መብት ትርጉሙ፤  ነገር ዓለሙ ያስቃል
አፍ ተለጉሞ በዝሙ፤ ጥርስ ከፍቶት ይስቃል።

**ወገንተኛ**
አልገዛም ያለው ወልቃይት ሲገዛ
ወይዘሮ አዘብ መስፍን ይሉኝታን አውግዛ
አቅመ ቢስ ወግኗን ወንድ ወንዱን አግዛ፤

ወይዛዝርቱን ሳይቀር አውጥታ ከጓዳ
ባላልቦ አረገችው ሁሉን ባለማርዳ።
ግንቦት 2007
አብርሃም በየነ